# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

## የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ /2015
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
# የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የ2015 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ የተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

## 1. ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)፤

1.1 የተጣራ ሀብት በሂሳብ መደብ 5601 (7111101) ብር 353,621.91 ከመደበኛ የሂሳብ ሚዛን ውጭ በዴቢት የታየ መሆኑ፤

1.2 በድምሩ ብር 312,211.00 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

1.3 ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ በየበጀት አርዕስቱ የተመደበው የተስተካከለ በጀት እና ሥራ ላይ የዋለው ከ10% (በመቶ) በላይ የሆነውን ንጽጽር በማድረግ ሂሳቡ ሲመዛዘን ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 3,474,587.64 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

## 2. የሕጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)፤

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ-12 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማንኛውንም ስቶክ ሲቀበሉ ማድረግ ያለባቸው በፌደል ለ/የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሳከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የተገዙ ዕቃዎች በመመሪያው መሰረት በጥራት ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ተረጋግጠ ገቢ ተደርጎ ክፍያ ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምሩ 3,055,452.34 ለአቅራቢዎቹ ክፍያ ሲፈፀም ንብረቶቹ በትክክል በተፈለገው ዝርዝር (specification) መሰረት መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

## 3. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፤

### 3.1 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት ባለስልጣን መስሪያቤቱ የተሸከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በመመሪያው መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ታርጋ ቁጥር 4-28752 እና 4-00465 የሆኑ ተሽከርካሪዎች የድሮው የመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ (ጉርድ ሾላ የሚገኝ) ያለአገልግሎት መወገድ ሲገባቸው ሳይወገዱ ለረዥም አመት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣

- ታርጋ ቁጥር 4-402 ሞተር ሳይክል ያለአገልግሎት በንብረት መጋዘን ውስጥ ቆሞ የሚገኙ  መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

### 3.2 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌላ መ/ቤት ስም የሚገኝ መሆኑ፤

በባለስልጣን መ/ቤቱ 5 (አምስት) መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌላ መ/ቤት ስም ተመዝግበው የሚገኙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

**ታህሳሰ 2015**